# አድዋ!

የጥቁር ሕዝብ ገድል ታሪክ አምባ፤
አዲስ ምዕራፍ የፃፈች ደም - አቅልማ ነጫጭባ። የጐንቻው!



አድዋ አምባ ምድር ፋሺሽት ቢረግጠው፤
ጠጉረ ልውጥ ጠላት ጣሊያን ቢደፍረው፤
ተጣራ ተራራው ቀሮ'ት ውቃቤው፤
ከአራቱ ማዕዘን ጀግናው ተፎካከሮ፣
በቅሎውን አላብሶ፣ ጋሻውን ጠድሮ፣
ጥምጣሙን አዞሮ፣ ሳንጃውን ወድሮ፤
ውጅግራውን ስቦ ለቨኑን ወልውሎ፤
ወገቡን ጠምጥሞ ዝናሩን አውሎ፤
ትከሻውው ጀበርና በደረቱ አማክሎ፤
የጥንት የአባቶቹን ፈለግ ተከትሎ፣
ሽቅብ ኢጋመረ ሰደድ ተቀጣጥሎ፤
እየተወባራ ዘራፍ ብሎ ጃሎ፤
በየመሪው ሆኖ አንበሳው አገሳ፤
አበሻው ሆ! ብሎ ዳር-ከዳር ተነሳ።



መላ አውሮፓዊ የነጭ ዘር ዶልቶ፣አገር በቅርጫ በልቶ፣
እንግሊዝ፣ ጣሊያን፣ ስፓኝ፣ ፈረንሳይ፣ፓርቹጋል ጓጉቶ፣
መላ አፍሪቃን ሊገዛ፣ ተቀራምቶ፣ ከነዜጐቿ ቀምቶ፣
ውል ሽርበ ሴራ በኃይሉ ተመክቶ በትዕቢቱ ተንጠራርቶ።

ከፈጣሪ ፈቃድ ከአምላክ አፈንግጦ፣
የብስ ባህር አልፎ ጠፈር አቆራርጦ፣
በገፍ ጦሩን ጭኖ መርዝ ጦስ በጥብጦ፣
ቀፈት ከርስ ሊሞላ የሰው ቤት ቀላውጦ፣
ደም በከንቱ ሊያፈስ ለቅኝ ግዛት ቋምጦ፣
ሰው ሊሸጥ ሊሸቅጥ ' ባሪያ' ብሎ እረግጦ፣
ከአምላካችን ግርጌ በሰማያት ጠድፎ፤
ግፍ አዘነበ ቦምብ ጢስ መርዝ አርከፍክፎ፤
ጥቁር ደም አበላ የግፍ ጽዋ አጉርፎ፤
ጠራርጐ ወሰደው አፈር ምድሩ ቀስፎ።

ጥንት አገር ኢትዮጵያ፤ የ'አቢሲኒያ' ቅርጫ፤
ቁርጥ ልትሆን ዳረጐት ለፋሽስት መፈንጫ፤
በነጮች ቅርምት በስለት ተውግታ፤
ሺኸር፤ ሙከታቸው ሊያመክኗት ታግታ፤
ታሪክ አንደነቷን ባህል ሕዝቧን ንቆ፣
ጣሊያን በቆየ ቂም ሴራውን አርቅቆ፤
መንጋ ነጫጭባ' 'ደባ ውል' አጺድቆ፤
በውጫሌው አንቀጽ ሊያስረን ሲል ሸምቅቆ፤
እምቢ አሉ እቲጊያችን 'ጣይት' ሴት እንቆቆ።

በአፈሯ በአየሯ ሻቅሎ ሰክሮ ኑሮ፣
ንጉስ ፤ ቄስ፤ ሕዝባቸው አሲሮና መክሮ፣
ቀለብ፤ ትጥቅ ኮተቱን በመርከቡ ቋጥሮ፣
ገባ በ'መሰዋ' ቀይ ባህር ተሻግሮ።

# አድዋ!

የጥቁር ሕዝብ ገድል ታሪክ አምባ፤
አዲስ ምዕራፍ የፃፈች ደም አቅልማ ነጫጭባ። *የጉንቻው!*

ጩካኝ ጀነራቾች፤ የጦር አዛዥ መርጠው፤
'አልበርቶኒ'፣ 'ባርቴሪ' ሃያ-ሺህ ታጅበው፣
የግብፆችን ዱካ ፈለግ ተከትለው ፤
በ ኢስማል መቃብር በ 'ጉራ' ተሻግረው፤
ሞት ጠርቷቸው መጡ፤የሰው አገር ናፍቀው፤
በዮሐንስ ግዛት በጀግኖቹ ጎራ፤
ጸብ ሸተው መሸጉ በአዲግራት ተራራ።

ቃል ሰጥቷልና ለሮማው ገዥ በደርሶ መልሱ፣
'አበሻን' ፈጅቶ ንጉሱን ሊያቀርብ ከነነፍሱ፣
አፄ ምንይልክን በ'ሸቦ ቅርጫት' አስረው ሊያደርሱ፣
ለመዝናኛ መጫዎቻቸው በሮም ሀገር ለንጉሱ፣
እንዲህ ነበር ንቀው ተሳልቀው 'አድዋችን' የደረሱ፤
በራሳችን በአገራችን እልቆ ጦር ሰብቀው የኰነሱ።

ይኸንን ቢሰሙ የሸዋው ንጉስ አባደፋር፣
አፄ ምንይልክ የአንበሳው አምሳል የአበሻው ዘር፣
ከተት አወጁ እያስጐሰሙ ነጋሪት እያስነረቱ ከበሮ፣
እቴጌም ጣይቱ አሰናድተው ስንቅ ግብር ድንኳን በጓሮ፣
ተከተለኝ አሉ በቁርጥ ቀን ንጉሥ ከአገሬው መክሮ ዘክሮ፤
እሙን ሆነ፤ የነጻነት፤ የሰማዕታት፤ የፃድቃኖች ቀነ- ቀጠሮ።

አድዋ አምባ ምድር ፋሺስት ቢረግጠው፤
ጠጉረ ልውጥ ጠላት ጣሊያን ቢደፍረው፤
ተጣራ ተራራው ቀፎ'ት ውቃቤው፤
ከአራቱ ማዕዘን ጀግናው ተፎካከሮ፣
በቅሎውን አላብሶ፣ ጋሻውን ጠድሮ፣
ጥምጣሙን አዞሮ፣ ሳንጃውን ወድሮ፤
ውጅግራውን ሰቦ ለቨኑን ወልውሎ፤
ወገቡን ጠምጥሞ ዝናሩን አውሎ፤
ትከሻው ጀበርና በደረቱ አማክሎ፤
የጥንት የአባቶቹን ፈለግ ተከትሎ፣
ሸቅብ ኢጋመረ ሰደድ ተቀጣጥሎ፤
እየተወባራ ዘራፍ ብሎ ጃሎ፤
በየመሪው ሆኖ አንበሳው አገሳ፤
አበሻው ሆ! ብሎ ዳር-ከዳር ተነሳ።

የራስ መኰንኑ የሐረሩ ጦር፣
አልፎ 'ወራይሉ' ደርሶ በግምባር፣
በ 'ዶጋሌ' መልካዓ የራስ መንገሻው፣
የ'ዮሐንስ' በኩር የትግራይ መሪው፣
ደፍጦ 'አምባለጌ' ላይ ጠላቱን ፈጀው።

የ 'ተክለ ሃይማኖት' የ 'ጐጃሙ' አርበኛ፣
የ 'ራስ ሚካዒሉ' የወሎው' ቁርጠኛ፣
የኢትዩጵያ መድኅናኖች የጠላት መጋኛ፤
በሦስቱ ማዕዘን ሲቆሰቁስት ሲያርገበግቡት፣
ቆልተው ሲያሳርሩት አቃልጥለው በአፎት፣
አፄም ምኒልኩ፣እቴጌ ጣይቱ ደርሰው በጠዋት፣
ተሳልመው ተማጽነው 'አባ ገሪማውን' ገድሉንታቦት።

# አድዋ!

## የጥቁር ሕዝብ ገድል ታሪክ አምባ፤
## አዲስ ምዕራፍ የፃፈች ደም አቅልማ ነጫጭባ።

የጎንቻው!

ነጭ ሻማ ለብሰው ሊቀ መኳስ መርተው፣
አሹነ ማቲወስን ደጀን አስከትለው፣
ባርከው ቀደሱለት መሃል ጦሩን ገብተው፣
ከጠላት ከንድተው ውጊያ ስልት ነድፈው፣
ከፊትና ኋላ ከበው አቋራርጠው፣
አደነባበሩት ሁለት ብርጌድ ከፍለው።

የአልበርቶኒውን ጦር ሸጥ በሸጥ አሳደው፤
የባርቴሪንም ጦር ጉሮሮውን ዘግተው፣
የአበሻው ባለሟል በልጠውና ጠብበው፤
የውጊያው ሊቃውንት አገር ያፈራቸው፣
ጥቁሩ ሰው ምንይልክ ጣሊያን ቢንቃቸው፤
ነጮቹን አኮሰሰው አመድ አረጓቸው።

ቀበሌው በሩምታ በቀውጢው ሲሻማ፣
ጋራው ሲናቃነቅ በመድፍ ሲያግማማ፣
ሰማይ በጢስ ዳምኖ ቀን ሲሆን ጨለማ፤
ምድር ቀውጢ ሲሆን አቧራው ሲነሳ፣
ተቆላልፎ ሲወድቅ ሬሳ በሬሳ፣
አየሩ ባሩዱ ወበቅ ሲከረፋ፣
አሞቱ ሲንጫረር ሳቶኑን ሲተፋ።

'የጦሩ ገበሬ' ገባ እየፎከረ፣
በጐራዴው አንገት እየሰባበረ፣
በሳንጃው ሆድእቃ እየበረበረ፤
ደም ጠምቆ ጠላቱን ግቶ እያሰከረ፤
ኃያሉ አበሻ ገድሉን አበሰረ፣
የአያት ቅድመ አይቱን ድሉን አዘከረ።

ከምድር ወደ ሰማይ ትዕንግርቱ ያለፈ፤
በከዋክብት ፊደል ብዕራና አስጠለፈ፤
የዓለም ሕዝብ ተማረ አበሻ አሸነፈ፤
የጥቁር ሕዝብ ገድል በነጭ ደም ተፃፈ፤
በዓለም አደባባይ አድዋ ገዘፈ።

በ 'ኢሻሾ'፣ ' ባላህ' በአድዋ ቋጥኞች፤ ሸለቆ ተራራ፣
ዶጋሌ፤ አምባለጌ፤ በቦሩ ሜዳ ላይ አፅሙ የተዘራ፣
በየ 'መልከዓ'ው ውለው የተሰውት ጀግኖች ታላቅ ገድል ሥራ፤
ሆኖ ይከበራል ትውልድ የሚያኮራ።

ሺህ ጠላቱን ገድሎ አሳዶና ማርኮ፣
ኃያሉን ወራሪ የረታ አፍረክርኮ፤
አስገበረ ካሳ በውል አንበርክኮ፤
ደም አፈሩን ሆኖ ነፍሱ የጸደቀ፣
ጀግናው ማንነቱን በዓለም ያሳወቀ፣
ድንበሩን፤ ወገኑን ክብሩን ያስጠበቀ፣
ከ'አንበሶች መንጋጋ' ክብሩን የነጠቀ፣
ለመላው ጥቁር ዘር ጐህ አስፈነጠቀ ።

ጀግናው ታሪክ ክብሩን አንድነት ሰንድቆ፣
ትውልድ ከትውልድ ወዳጅ ጠላት አውቆ፤
ኢትዩጵያዊ ይኑር ቃልኪዳኑን ጠብቆ ።

117ኛው የአድዋ በዓል መታሰቢያ ፤ የካቲት 23 ቀን 2005 ዓ.ም
የጎንቻው!

yegonchaw@yahoo.co.uk